# በውንጀላ የተካነው ሰማያዊ ፓረቲ

**ይሁን ባንተያምረል**

**02-27-15**

ተቃዋሚነት ማለት የጥላቻ ፖለቲካ ማራመድ ወይም መሰረተቢስና ጭፍን የማጥላላት ዘመቻ ማካሄድ ማለት አይደለም:: ከዚህ ይልቅ ተቃዋሚነት ማለት በምክንያት ላይ ተመስርቶ ገዥውን ፓርቲ መሞገት፣ አዎንታዊ ጅምሮችን እውቅና በመስጠት የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚችሉ ማሳመን፣ ስህተቶችን ወይም ጉድለቶችን ደግሞ በግልጽና በተጨባጭ ማስረጃ በማቅረብ መተቸትና አማራጮችን ማመላከት መሆን መቻል አለበት፡፡

አሁንም ሆነ ቀደም ሲል ግን ከአብዛኞቹ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ይህን ሚዛናዊና ምክንያታዊ የሆነ አመለካከት እያየን አይደለም፡፡ በተለይ የዳያስፖራ ፖለቲከኞች የአገራችንን የዴሞክራሲ ስርዓት ሆን ብሎ ለማፍረስ ይመስለኛል። አንድ የሀገራችን ታላቅ አርቲስት እንዳለው የሁሉም ነገር መሰረቱ አገር ነች። "…በሀገር ነው ሁሉም በሀገር ነው፡፡" ዛሬ የምንፋቀረው፣የምንስቅ የምንጫወተው የምንጨቃጨቅ የምንዘላለፈው አገራችን በመኖሯና ነፃ በመሆኗ ነው። እውነት ነው፤ሁሉም የሚያምረው በአገር ነው፡፡ታዲያ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው እንሰሳ እንዲህ ያለ ቅጥ ያጣ ነገሮች አግባብ አይደለም።

እንደ አንድ ሀገር ወዳድ ዜጋ እያየሁ ያለሁት አንዳንድ አካሄድ ግን ለአገርና ለህዝብ ይጠቅማል ብዬ ስለማላስብ ይህችን መልዕክት ላደርሳችሁ ወደድኩ። አንዳንድ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የሚያደርጉት እንቅስቃሴና፤ በምርጫ የህዝብን ቀልብ ለመሳብ ሲሳናቸው ተብሎ እየተደረገ ያለው የማደናገር ሥራ ሁሉ ሆንብሎ ከማጥላላት አባዜ የመነጨና በዚህም ህዝብን ውዥንብር ውስጥ በመክተት ርካሽ ዓላማን ለማሳካት ካለ ፍላጎት የተነሳ ነው የሚል ዕምነት አለኝ።

ይህ ደግሞ በተጨባጭ የሚታይ ዕውነታ ቢኖርም እኔ "የለም" ካልኳችሁ "የለም ማለት ነው" ወይም "የምላችሁን እንጂ የምታዩትን አትመኑ" የሚል ከጭፍን አመለካከት የሚመመነጭነው።ታዲያ እንዲህ ያለውን ሰው የአዕምሮ ጤንነቱን ሁኔታ ከመጠራጠር ባለፈ ምን ሊባል ይቻላል?

በአገራችን ስለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች መረጃ ለማግኘት በአብዛኛው የአገር ውስጥ የግል ጋዜጦችንና የውጭ ሚዲያዎችን በብዛት እከታተል ነበር። በቅርቡም ከምርጫ 2007 ጋር ተያይዞ አንዳንድ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምረጡኝ ዘመቻ በፊት የሚያነሷቸውን ጉዳዮች ስመለከታቸው ቀድመው ሸንፈታቸውን በመረዳታቸው የምርጫውን ሂደት ለማጣጣል የተነሱ ያስመስላል።

አንዳንድ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ሁለት አማራጭ ይዘው ወደ ምርጫ ውድድር ለመግባት የፈለጉ ይመስለኛል። እነዚህ አካላት ውድድሩን በሰላማዊ መንገድ የሚያሸንፉ ከሆነ ጠንካራ በመሆናቸው በህዝብ ይሁንታ ስልጣን እንደያዙ አድርገው ይፎክሩበታል። በሌላ በኩል  በምርጫ የማያሸንፉ መስሎ ሲታያቸው የተለያዩ ዘዴዎችን በመደርደር ስህተታቸውን ሁሉ በሌሎች ለመደፍደፍ ሴራ ሲያስሩ የሚውሉና የሚያድሩ አንደሰማያዊ ፓርቲ ያሉ ፓርቲዎች አሉ።

የእንደዚህ ያሉ ፓርቲዎች አንዱ መንገድ የምርጫ ሂደቱን በማጣጣል ለአብነት  የፖለቲካ ምህዳሩ ፍተሃዊ አይደለም፣ ምርጫ ቦርድ እንዲህ ነው፣ መንግስት እንዲህ አደረገን፣ ገዥው ፓርቲ ይህን አደረገ ወዘተ ያሉ በማለት ከምርጫ ሰላማዊ አካሄድ የወጣ እንቅስቃሴ ማሳየታቸው ተገቢ አይመስለኝም። እናም የእነዚህ የአንዳንድ ፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች አካሄድ የተመለከተ አንድ ወዳጄ  እነዚህ ሰዎች የፕሮሶፓግኖሲያ (Prosopagnosia) ተጠቂዎች የሆኑ ይመስል ለምን ለትንሹም ለትልቁም ነገር ሰበብ ይፈልጉለታል፡፡ ይህ ወዳጄ የተጠቀመበትን ቃል ከዚያን ቀደም ሰምቸው አላውቅም ነበርና በዚህም ምክንያት ቃሉን እንኳ ደግሜ ለማለት እያቃተኝ ትርጉሙን እንዲያብራራልኝ ጠየኩት፡፡

ፕሮሶፓግኖሲያ (Prosopagnosia) ማለት ፈረንጆች ''face-blindness'' የሚሉት ነው፣ አለና ቀጠለ፡፡ ይህም ማለት አንድ ሰው በሚገባ የሚያውቀውን ሌላ ሰው በአካል በመመልከት ወይም የሰውዬውን ምስል በፎቶግራፍ ይሁን በስክሪን ወይም በሌላ አይቶ ማንነቱን በትክክል ለመለየትና ለማወቅ ያለመቻል ከነርቭና አዕምሮ ጋር የተገናኘ የጤንነት ጉድለት ወይም ችግር መሆኑን ነገረኝ፤ ከዚህ በባሰም ይህ የጤና ችግር የሌላ ሰውን ገጽታ ብቻ ሳይሆን በፎቶግራፍም ላይ ሆነ በመስታዎት ውስጥ የሚታይን የራስንም መልክ ወይም ገጽታ ፈጽሞ እስካለመለየት የሚያደርስ እንደሆነም አጫወተኝ፡፡ ደግነቱ ይህ ህመም ሰፊ ስርጭት የሌለው መሆኑና  በዚህ ህመም የሚሰቃዩ ሰዎች ቁጥር በዓለም በመቶዎች ብቻ የሚቆጠሩ በመሆናቸው እንጂ የሚያስከትለው ማህበራዊ ቀውስ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም ነበር።

አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይ የዳያስፖራ ፖለቲከኞች ባለፉት ጥቂት ዓመታት በዚህች አገር የተመዘገቡ በርካታ የዕድገትና የልማት ስኬቶችንና መሬት የረገጠ ተጨባጭ እውነታን አምኖ አለመቀበልና ቢያንስ  ዕውቅና አለመስጠት ከዚህ የጤንነት ችግር በምን ይለያል ትላላችሁ? ፕሮሶፓግኖሲያ የጤንነት ችግር ባይሆን ኖሮ ''ዐይኔን ግንባር ያድርገው'' ከሚለው የአገራችን አባባል ጋር የሚመሳሰል ይመስለኛል።

አሁን ያለንበት ወቅት አንድ ታላቅ አገራዊ ጉዳይ የሚፈጸምበት ዋዜማ ወይም መዳረሻ ላየ ነን:: የዜጎች የሥልጣን ባለቤትነት ማረጋገጫ የሆነው ምርጫ 2007 ሁሉም በጉጉት የሚጠብቀው ታላቅ አገራዊ ክንውን በመሆኑ ዜጎች በቀጣይ አምስት ዓመት አገርና ህዝብን የሚመሩ ተወካዮቻቸውን የሚመርጡበት ወቅት ነው። አገራችን የጀመረችውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና ፈጣን እድገት ልናስቀጥል የምንችለው ይወክለናል የምንለውን መንግስት በምርጫ ማቋቋም ስንችል ብቻ ነው።

በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ጠንካራ መሰረት ሊይዝ የሚችለው በህዝቦች ይሁንታ የሚመሰረት መንግስት ሲቋቋም በመሆኑ ለዚህ ደግሞ ዋንኛው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ የግድ ይላል። ዴሞክራሲያዊ  ምርጫ ወቅትን

ጠብቆ እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የሚካሄድ ህዝብ ተወካዮቹን የሚመርጥበት፣ በሰላማዊ መንገድ መንግስት የሥልጣን ሽግግር የሚደረግበት፣ የሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብት ማለትም የመምረጥ እና የመመረጥ መብት የሚተገበርበት ሂደት ነው፡፡

ምርጫ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲ፣ ለልማትና መልካም አስተዳደር መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ሲሆን ለሌሎች ሰብዓዊ መብቶች መከበርና መሟላት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሂደት ነው፡፡ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 38 እንደሚደነግገው የዜጎችን የመምረጥና የመመረጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንደሆኑ ሁሉ የመንግስት ስልጣንም በቋሚነት የሚመነጨው በየአምስት ዓመቱ በሚካሄድ ምርጫ እንደሆነ ይደነግጋል። ይህን የህግ ማዕቀፍ መነሻ በማድረግም እስካሁን በአገራችን በተካሄዱት አራት አገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች ከፍተኛ ህዝባዊ ተሳትፎ የታየባቸው በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉባቸው ነበሩ፡፡ የአገራችን የምርጫ ባህልም ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ እንደመጣም ማየት ይቻላል። አገራችን በያዝነው አመት ለአምስተኛ ጊዜ አጠቃላይ ምርጫ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ትገኛለች። የዘንድሮውን ምርጫ እንደቀድሞዎቹ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎች በመከናወን ላይ ነው።

ምርጫ በአንድ አገር የዴሞክራሲያ ስርዓት መጎልበት የማይተካ ሚና የሚጫወት ከመሆኑም ባሻገር ለዘላቂ ሰላም መስፈን፣ ቀጣይነት ላለው ልማት መፋጠን እንዲሁም ለመልካም አስተዳደር መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጸዖ ያበረክታል፡፡ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታም ምርጫ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ህገ መንግስቱ በሰጣቸው መብት መሰረት በህግ በልዩ ሁኔታ የታገደ ካለሆነ በስተቀር ዜጎች የዘር፣ የሃይማኖት፣ የጾታ ወዘተ ልዩነት ሳይደረግባቸው በነጻነትና በሚስጥር ይወክሉናል ይበጁናል የሚሏቸውን ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የሚችሉበትን ተወካዮቻቸውን የሚመርጡበት ሂደት ነው፡፡

ግንቦት 16 ቀን 2007 የሚካሄደው ይኸው 5ኛው አገር አቀፍ ምርጫ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ማለትም የዕጩዎችና የመራጮች ምዝገባ ተጠናቋል:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመራጭነትና በተመራጭነት የሚሳተፉበትን ይህን ታላቅ ክንውን ለማሳካትም በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፤እየተከናወኑም ሲሆን ቀሪ ሥራዎችም በተያዘላቸው የአፈጻጸም መርሃ ግብር መሰረት በቀጣይ ተፈጻሚ ይደረጋሉ፡፡

መንግስት አቅም በፈቀደ መልኩ ለምርጫው ስኬታማነት የሚያግዙ ነገሮችን ከሚመለከታቸው አካላቶች ጋር በማከናወን ላይ ይገኛል። በዋናነትም ሕጋዊ ዕውቅና ኖሯቸው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለሚያራምዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የምርጫ መወዳደሪያ መድረኩ ክፍት መሆኑ እንደ መነሻ የሚወሰድ ሆኖ፣የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ መውጣቱ፣ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጎማ መደረጉ፣ ለምረጡኝ ቅስቀሳ ነፃ የሚዲያ የአየር ስዓትና የጋዜጣ አምድ መሰጠቱ፣ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከደጋፊዎቻቸው ጋር በነፃነት ተገናኝተው እንዲወያዩና ራሳቸውንና ዕጩዎቻቸውን እንዲያስተዋውቁና ድጋፍ እንዲያሰባስቡ መደረጉ፤ ማናቸውንም ቅሬታና አቤቱታ በሰላማዊና ሕጋዊ አግባብ በየደረጃው ለመፍታት የሚያስችሉ ስልቶች በፓርቲዎች የጋራ ስምምነት ፀድቀው ተጋባራዊ መደረጋቸውና ለዚህ

የሚረዳም የጋራ መድረክ መፈጠሩ እንደ እኔ ታላቅ ግምት ሊቸረው የሚገባ ነው፡፡ እንደኔ መንግስት የዴሞክረሲ ስርዓት በአገራችን እንዲጎለበት ከሚያደርጋቸው ተግባራት መካከል አንዱ ተግባር ይመስለኝል።

የመንግስት ስልጣን በወቅት እንዲወሰን መደረጉ፣ የስልጣን ብልግና እንዳይኖር ያደርጋል። በምርጫ ያሸነፈ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ከህዝብ ጋር የአምስት አመት የኮንትራት ውል በመፈራረም መንግስት ይመሰርታሉ። በ2002 ዓ ም አሁን ያለውን መንግስት በምርጫ ስንመሰርት የሰጠነው ሃላፊነት የአምስት ዓመት በመሆኑ፣ ይህ ኮንትራት ደግሞ የሚጠናቀቀው በያዝነው አመት መጨረሻ በመሆኑ ለቀጣይ አምስት አመታት ህዝብና አገርን የሚመራ መንግስት ለማቋቋም አዲስ ምርጫ የምናካሄድበት ወቅት ነው።

በቀጣዩ ምርጫ አሸናፊ ሆነው መንግስት ለመመስረት የሚያስችል ድምጽ ለማግኘት ወደ 65 የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመወዳደር በዝግጅት ላይ ናቸው። የብሄራዊ የምርጫ ቦርድ በአገሪቱ የሚካሄዱትን የተለያዩ ምርጫዎች እንዲመራ በህግ ሃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነው። የብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ከየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ሊወግን የማይችል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ገለልተኛ ተቋም ነው። ይህ ተቋም በአገሪቱ የሚካሄዱ የተለያዩ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊና በህብረተሰቡ ታዓማኒነትን ያተረፉ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል፤ አሁንም እየሰራ ነው።

በተለይ በምርጫ ወቅት በእኛ አገር የተለመደና ሆን ተብለው የሚነዙ አንዳንድ አፍራሽ አካሄዶች ለማንም የሚበጁ አይመስለኝም። በመርጫ የሚወዳደር አካል የአገሪቱን ማንኛውንም ህጎች የማክበርም ሆነ የማስከበር ሃላፊነት አለበት። ወደ ምርጫ የሚገባ አካል ሁሉ ሁለት አማራጭ ብቻ እንደሚኖረው መታወቅ ይኖርበታል። አንድ ማሸነፍ አሊያም መሸነፍ ናቸው።

አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከእነዚህ አማራጮች በተለየ ተጨማሪ የሚሏቸውን አማራጮች ይዘው በመቅረብ ነገሮች ወዳልተፈለገ መንገድ እንዲሄዱ ያደርጋሉ። ለዚህ እንደጥሩ ምሳሌ መነሳት ያለበት የቀድሞው ቅንጅት በምርጫ 97 ወቅት ይከተለው የነበረውን አካሄድ ማንሳት መልካም ይመስለኛል። አሁን ደግሞ እንደእኔ እይታ ሰማያዊ ፓርቲ ይህችን መንገድ እያማተራት ይመስለኛል። ምርጫውን ለማጣጣል ሲባል በምርጫ ሂደቱ ላይ ጥርጣሬ ለመጫር የሌሉ የፈጠራ ውንጀላዎችና ክሶችን ሲደረድር ይታያል። የምርጫ ቦርድን ታዓማኒነት ለማጠልሸት ሲባል የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት በምርጫ እንዳልወዳደር ተከለከልኩ በማለት በአንዳንድ ሚዲያዎች ሲናገሩ ይደመጣሉ።

የተከበሩ ኢንጂነር ለመሆኑ እውነታው ይህ ነውን? እርሶ ከምርጫ እንዲወጡ ማድረግ የሚችል አቅም ያለው ሃይል ከቶ ሊኖር እንደማይችል እርሶ ጠንቅቀው የሚያውቁት ይመስለኛል። ነገር ግን እርሶን ከምርጫ ውጭ ያደረጎት የአገሪቱ የምርጫ ህግ በሚያዘው መሰረት በግልጽና ማንም እውነታውን በሚያውቀው መንገድ ነው።

የምርጫ ህጉ በሚያዘው መሰረት በአንድ የምርጫ ጣቢያ መመዝገብ ካለበት ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር ከ12 ከዘለለ በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት እጩዎች በእጣ የሚለዩበት አካሄድ እንዳለ ህጉ ይደነግጋል። እርሶም ከሌሎች ፓርቲ እጮዎች ጋር በእጣ ተወዳድረው፣ በዕድሉ ተሸንፈው ከውድድር ወጡ እንጂ የምርጫ ቦርድ ወይም

በሌላ አካል ጫና ከምርጫ እንዳልወጡ እያወቁት እውነታውን መካድና ያልተገባ ምክንያት ማቅረብዎ ተገቢ አካሄድ አይመስለኝም።

አንድን ሕገ-ወጥ ድርጊት ማንም ይፈጽመው ማን በሕጉ መሰረት ተጠያቂነት እንዳለበት ማወቅ ተገቢ ነው። ሙብት ተጠያቂነትም እንዳለበት ይታወቃል። የፖለቲካ ፓርቲ ካባ ደርቦ የሕገ-ወጥና የወንጀል ድርጊት ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን የህግ ጥሰትን ማደፋፈር ከቶ አይቻልም፡፡ መሰረተ ቢስ ውንጀላዎችን በመደርደር በህዝብ ተቀባይነት ማግኘት አይቻልም። እንዲህ ያሉትን ህገ ወጥ አካሄዶች እያንዳንዱ ሰላም ወዳድ ህብረተሰብ በጽናት ሊያወግዘውና ተመሳሳይ ድርጊቶችም እንደይፈጸሙ ከወዲሁ ሊዋጋው ይገባል፡፡

በተለይም በምርጫ ዋዜማ ላይ ሆኖ እንደዚህ ዓይነት የበሬ ወለደ ማደናገሪያዎችን መደርደር በአገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲ ስርዓት ሊጎዳ የሚችል ነገር ማከናወን ሁላችንም በጽኑ ልንዋጋው ይገባ ድርጊት ነው፡፡ ይህን መሰል ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ እንዲካሄድ ማንም ሰላም ወዳድ ሕዝብ አይፈልግም፤ ድርጊቱም ለምንም ዓይነት ዓላማ ማስፈጸሚያነት እንዲያገለግል ሊፈቀድ አይገባም፡፡

ህዝብንና አገርን የመምራት ታላቅ ኃላፊነትን ለመሸከም ዓላማ ይዞ የሚንቀሳቀስ የፓርቲ አመራር ይህግ የበላይነትን በመጠበቅና በማስጠበቅ ረገድ ከማንም በላይ አርአያ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡ በምርጫ ለመወዳደር መጀመሪያ የአገሪቱን የምርጫ ህግ ማክበር ተገቢ ነው። ህግና ስርዓትን በመጣስ በምንም መልኩ ቢሆን ዘለቄታዊና ህዝባዊ ዓላማን ማሳካት አይቻልም፡፡ ሁለም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ብቻ ሰይሆኑ ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ ለህግ የበላይነት፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንና ለሰላም በፍጹም የኃላፊነት መንፈስ በጋራ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ወደ ምርጫ የሚገባ ሁሉ ሊያሸንፍ አይችልም።

የአመጽ፤ የሁከትና የሽብርተኝነት መንገድ እንደ አንድ የዓላማ ማስፈጸሚያ ስልት ለመጠቀም መሞከር ወንጀል ነው፡፡ በቅድመ ምርጫ 97 ወቅት ልቅ የሆነ የምረጡኝ ቅስቀሳ በአገራችን ምን ዓይነት ጥፋት፣ ጉዳትና ውድመት እንደደረሰ፤ይህን ተከትሎም ህግና ሥርዓትን ለማስጠበቅ ሕጋዊ እርምጃ እንደተወሰደና የዚያ የጥፋት ድርጊት ቀስቃሾች፣አስፈጻሚዎችና ፈጻሚዎች ላይ ያስከተለውን የሕግ ተጠያቂነት “ልብ ያለው ልብ ሊለው ይገባል” ፡፡ ዛሬም ያን አይነት ስህተት እንዳየደገም፣ ሰማያዊ ፓርቲ አካሄዱን ቀድሞ ሊያስተካክል ይገባል። ሞኝን እባብ ሁለቴ ነከሰው ይባላል፣ አንዴ ሳያይ ሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ሲያሳይ ይባላል። እኛም አገራችን ዳግም እንድትታመስ ወደ ሁከት እንድታመራ ማድረግ የለብንም።

የፖለቲካ ሥልጣን የሕዝብ ሥልጣን ውክልና እንጂ ማንም የፖለቲካ ድርጅት፣ቡድን ወይም ግለሰብ በራሱ የሚፈጥረውና የራሱን ፍላጎት በሌሎች ላይ በኃይል ለመጫን የሚጠቀምበት መሳሪያ አይደለም፡፡ በተለያየ ምክንያትና ሁኔታ በምርጫ አፈጻጸማቸው ላይ ችግር የተፈጠረባቸው ሀገራትና ውጤቱንም ተከትሎ የተከሰቱ የአመጽ፣ የሁከት፣ የጥፋትና የውድመት ምሳሌዎች እንደ ጥሩ ተሞክሮ ሊወሰዱ አይገባም፡፡ አንዳንድ ሰላማዊ ትግልን እንከተላለን የሚሉ አካላት በሁከትና በነውጥ የታጀቡ ምርጫዎችን ማለትም እንደ ዙንባቡዌና ኬንያ የተካሄዱ ምርጫዎችን ተሞክሮ

እንደመልካም መጥቀስ መልካም ጅምር አይመስለኝም። በየትኛውም መገድ ያለመግባባት ቢከሰት በመነጋገር ችግሮችን መፍታት የሰለጠነ አካሄድ ነው። ችግሮችን በማራገብ፣ የሃሰት ውንጀላን በመደርደር፣ እኔ ብቻ ትክክል ነኝ ወዘተ በማለት የዴሞክራሲ ስርዓት ሊጎለብት አይችልም። ሰማያዊ ፓርቲ እንዲህ ያሉ ከምርጫ ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ቀድሞ በማጣጣል ስልት የተጠመደ ይመስለኛል።

ስለሆነም መላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዘንድሮውን ምርጫ በሁለንተናዊ መልኩ የተሳካ ለማድረግ በሚያስችል አኳኋን በምርጫው ያሳዩትን መነቃቃትና ተነሳሽነት እስከ መጨረሻው ይዘው መዝለቅ ይኖርባቸዋል፡፡ የአፍራሽ ኃይሎችን ግልጽና ስውር እንቅስቃሴ በትኩረት በመከታተልና በማክሸፍ የምርጫውን ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የተሟላ ማድረግ ይጠበቅብናል እያልኩ መልካምና ስኬታማ ምርጫ ለሁላችንም እየተመኘሁ እኔ እዚህ ላይ ልሰናበታችሁ፡፡ ቸር ይግጠመን!